# ለመምህር የኔሰው ገብሬ




# የ40 ቀን መታሰቢያ!

ልረሳህ አልችልም፤ ብረሳህ “ሞት ይርሳኝ” . .፣
ከዚህች ስቃይ ምድር አንተን ያሳረፈ፣
በወርቃማ ብዕር ግብርህን ያስጻፈ፣
በሚሊዮኖች ልብ ውስጥ ስምህን ያሰረፀ፣
ሕያው ግዙፍ ሀውልት በክብር ያስቀረፀ…፣
ብረሳህ ሞት ይርሳኝ !

እንዴትስ ይረሳል፤ ያንተ ሕያው ጥበብ፣ ያነተ ረቂቅ ሥራ፣
በሞትህ ታጅበህ፣ በናት አገር ምድር ሕይወት እምትዘራ !
ልጠይቅህ መጣሁ፣ በሃሳብ ተጉዤ. . .፣
ዕረፍት ካረክበት ከሰማያት ማማ፣
ወንድም ያገሬ ልጅ እስኪ ስማኝማ !
ሕያው ነፍስ ከስጋ እስክትሄድ ተላቃ፣
ኤሎሄ! ኤሎሄ! . . . ጥሪው እስኪያበቃ፣
ሰቆቃ፣ ቃጠሎ. . . የስቃይዋ መዓልት፣
እንዴትስ አለፈች፣ ያቺ የጭንቅ ሰዓት?

ብረት-ለበስ ልቦች ብረት የታጠቁ፣
ዙሪያህን ከበውህ ሕዝብን ስያስጨንቁ፣
በጣዕር ስታቃስት፣ በሞት-በሕይወት መሃል፣
የነበርክበቱ “ወህኒ” ነው “ሆስፒታል”?
ማ! ቀና አደረገህ? ማን ውሃ አቀበለህ?
ውለታ እምንከፍለው፣ ማነው ያስታመመህ? !
ማተብ ያልበጠሰ፣ ለእውነት ያደረ፣
የኑዛዜ ቃልህን ማንስ ተቀበለ?
በጠመንጃ አፈሙዝ ፍትሃት ተደረገ?
ወይስ ቄስ ተገኘ ግብዓት ያሳረገ?

ለዘላለም ዕረፍት ርቀህ ከተለየህ፣
የሆነውን ሁሉ በቅርብ ስላላየህ፣
ይልቅስ ልንገርህ፣ መዋዕለ-ዜና ከምድር የተገኘ፣
ሞትህ ሕይወት ዘርቶ ባለም ዙሪያ ናኘ !
. . . በዓላማህ ጽናት መንፈሱ የራደ፣
በሕዝባዊ ቁጣ የተርበደበደ፣
መቃብርህ እንደ ሙሴ፣ እንደነ በዓሉ…፣
ሥፍራው ላይታወቅ እንዲጠፋ ውሉ፣
ሰማዕትነትህ ከቶ ላይወሳ፣
እንዳልባሌ ወግ ፍፁም እንዲረሳ…፣
እርኩሳን መናፍስት፣ ዛር የሰፈረበት፣
ለከት-የለሽ ጠላት ባልተገራ አንደበት፣
ሞክሮ ነበረ፣ ደብዛህን ለማጥፋት፤
አንተ ግን “የኛ ሰው” ! የመቃብርህ ሥፍራ፣
ባገር ልጆችህ ልብ በፅናት ተሰራ !





“እሳት ወይ አበባ”፤ አበባ ወይ እሳት… ፤
መምረጡ ተስኖን ከንቱ ስንዋትት፤
በየልባችን ውስጥ የተዳፈነውን፤
ኃያል ትኩሳቱን ገልጠኸው ረመጡን፤
የኔሰው መምህር የብርሃን ጮራ፤
ከጽንፍ-አጽናፍ ርቀት ሥምህ ደምቆ በራ!
እንደ ትንግርት ራዕይ የመለኮት ጸጋ፤
ሰብስበህ አሰርከው አበሻን ባንደጋ፤
ቆራጥ መስዋዕትነት ቢሹት እማይገኝ፤
ሞትህ ያገር ልደት ሊሆን ነው መሰለኝ!








ጌታቸው አበራ
ከምድረ-አፍሪቃ
ታህሳስ 2004 ዓ/ም
(ዲሴምበር 2011)

(በሕዝብ እና በአገር ላይ የሚደርሰውን ግፍና በደል በብርቱ በመቃወም፤ በውድ ሕይወቱ መስዋዕትነትን ለከፈለው ለመምህር የኔሰው ገብሬ መታሰቢያ)

EthioLion.Com